በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No 1/189/10
ቀን / Date 18 ነሐሴ 2010

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ ፡- <u>መመሪያ ስለመላክ፤</u>

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የወጣ የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 137/2010 ሥራ ላይ እንዲውል የተላከ መሆኑን አስታውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ዑመር ሁሴን አ...
... ዳይሬክተር /ሚኒስት...

<u>ግልባጭ</u>

ለአገር ውስጥ ታክስ ዘርፍ

ለጉምሩክ ዘርፍ

ለሕግ ማስከበር ዘርፍ

ለአቅም ግንባታና ሀብት አስተዳደር ዘርፍ

ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

ለዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን !!

ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet.et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ዳይሬክቶሬቶች፡-

- ለአገር ውስጥ ታክስ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ኦዲት ልህቀት ማዕከል ዳይሬክቶሬት
- ለየገቢ ሂሳቦች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ አስተዳደር ማጣጣምና የክልሎች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታስስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አሠራርና ድጋፍዳይሬክቶሬት
- ለአምራቾችና የወጪ ንግድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለሕግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለኦዲት አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለሥጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለኢንተሊጀንስ ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለኮንንትሮባንድ ክትትልና የዕቃ አወጋገድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት
- ለሴቶችና ወጣቶች ጉዳይ ዳይሬክቶሬት
- ለሥነ-ምግባር መከታተያ ዳይሬክቶሬት
- ለውስጥ ኦዲት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
- ለፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለጥናትና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለኦዲት ጥራት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት
- ለሰው ሀብት ሥራ አመራርና ልማት ዳይሬክቶሬት
- ለለውጥ ትግበራ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለሥልጠና ማዕከል
- ለትምህርትና ሥልጠና ዳይሬክቶሬት
- ለሥልጠና ማስተባበሪያና ግብዓት አቅርቦት ዳይሬክቶሬት

<u>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች፡-

- ለከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  አዲስ አበባ

- ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  አዳማ

- ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሞጆ

- ለባህርዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ባህርዳር

- ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  መቀሌ

- ለሀዋሳ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሀዋሳ

- ለድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ድሬደዋ

- ለኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ኮምቦልቻ

- ለሚሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሚሌ

- ለጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ጅግጅጋ

- ለሞያሌ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

  ሞያሌ

- ለጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጅማ
- ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጋላፊ

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

## የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ

## መመሪያ ቁጥር 137/2010

ነሀሴ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 2
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

# የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 137 /2010

ባለሥልጣኑ መቀጫ ይነሳልኝ ማመልከቻ ሲቀርብለት ወይም በራሱ ተነሳሽነት በታክስ ከፋይ ላይ የተጣለን አስተዳደራዊ ቅጣት በሙሉ ወይም በከፊል ሊያነሳ እንደሚችል የተደነገገ በመሆኑ፣

ታክስ ከፋዮች በልዩ ልዩ ምክንያቶች ግዴታቸውን በህግ በተመለከተው መሠረት መወጣት ባለመቻላቸው የሚጣልባቸው አስተዳደራዊ ቅጣት ታክሱን ለመክፈል ፈቃደኛ ቢሆኑም አስተዳደራዊ ቅጣቱ ካልተቃለለ በስተቀር የመክፈል አቅማቸው የሚዳከም በመሆኑ፣

አስተዳደራዊ ቅጣቶች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማንሳት ታክስ ከፋዮች ታክስ ከፋይ ሆነው እንዲቀጥሉ የሚያግዝና ውዝፍ ፍሬ ታክስን ሳይዘገይ ለመሰብሰብ አጋዥነት ያለው መሆኑ ስለታመነበት ወጥ በሆነ ሁኔታ አስተዳደራዊ ቅጣቶች የሚነሱበትን መስፈርት በማውጣት ፍትሃዊ አሰራርን ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 115(4) ላይ በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።



Ethiopian Revenues & Customs Authority Records & Documentation No.2

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ መመሪያ ቁጥር 137 /2010" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   ለዚህ መመሪያ አፈጻፀም የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፡-

   1. **"የታክስ ህግ"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(36) የተሰጠውን ትርጉም የሚይዝ ሆኖ የጉምሩክ ህግን አይጨምርም፡፡
   2. **"አስተዳደራዊ ቅጣት"** ማለት በፌዴራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 2(24) ላይ የተቀመጠውን ትርጉም የሚይዝ ሆኖ የወጪ መጋራት እና የጡረታ መዋጮ ግዴታን ባለመወጣት የሚጣል ቅጣትን አይጨምርም፡፡
   3. **"የታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል"** ማለት በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 55(1) በአዋጁ መሰረት በባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተቋቋመ፣ በግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት በአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ ላይ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ሲቀርብ በማጣራት ለቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ የውሳኔ ሃሳብ የሚያቀርብ የሥራ ክፍል ነው፡፡
   4. **"ሐራጅ/ጨረታ"** ማለት የታክስ ግዴታን ባለመወጣት በባለስልጣኑ የተያዘን ንብረት በግልጽ ወይም በዝግ ሥነ-ሥርዓት የመሸጥ ሂደት ነው፡፡
   5. **"ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት"** ማለት ታክስ ከፋዩ በራሱ ሊያስወግደው የማይችል ከፍተኛ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋ ወይም ጽኑ ህመም ወይም ታክስ የመክፈልና ሌሎች ግዴታዎችን የመወጣት ግዴታ እንዳይወጣ የሚያደረግ ተጨባጭ እና የተረጋገጠ ምክንያት ነው፡፡
   6. **"ጽኑ ህመም"** ማለት በታክስ ማስታወቂያ ጊዜ ውስጥ ተንቀሳቅሶ መስራት የማያስችልና በታወቀ የህክምና ተቋም ቢያንስ ታክስ ከፋዩ የውሳኔ ማስታወቂያ



Ethiopian Revenues & Customs Authority Documentation No.2

ከደረሰው ወይም አስታውቆ መክፈል ባለበት ጊዜ ውስጥ የሚያስተኛ ህመም ሆኖ በህክምና ማስረጃ የሚረጋገጥ እና የንግድ ስራ እንቅስቃሴውን የሚመራለት የታክስ እንደራሴ የሌለው ሲሆን ነው፡፡

7. "የቅጣት ደረጃ ምደባ" ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በከፊል የሚነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት ለመወሰን ሲባል በታክስ አስተዳደር አዋጁ ክፍል አስራ አምስት ምዕራፍ ሁለት ስር ከአንቀጽ 101-114 የተዘረዘሩትን አስተዳደራዊ ቅጣቶች ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ በማለት የተደለደለበት የቅጣት ምደባ ደረጃ ነው፡፡

8. “ባለሥልጣን” ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ገቢዎች ባለሥልጣንን ይጨምራል፡፡

9. “አዋጅ” ማለት የፌዴራል ታክስ አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 983/2008 ነው፡፡

10. በዚህ መመሪያ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሀረጎች እንደሁኔታው በታክስ አስተዳደር አዋጅና በታክስ ህጎች ውስጥ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፡፡

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዋጁ መሠረት በተጣለ በግብርና ታክስ አስተዳደራዊ ቅጣት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## አስተዳደራዊ ቅጣት የሚነሳበት ሁኔታ እና መጣኔ

4. አስተዳደራዊ ቅጣት የሚነሳበት ሁኔታ

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 እና 13 ድንጋጌዎች መሰረት አስተዳደራዊ መቀጫዎች ከማይነሱባቸው ሁኔታዎች በስተቀር ከዚህ በታች በተደነገገው መሰረት በአዋጁ የተጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች በከፊል ወይም በሙሉ ሊነሱ ይችላሉ፡፡

5. አስተዳደራዊ ቅጣቶች በከፊል የሚነሱበት ሁኔታ

በአዋጁ መሰረት የተጣለ አስተዳደራዊ ቅጣት የድርጊቱ መፈፀምና አለመፈፀም በታክስ አስተዳደር ስርዓቱ ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ እና የታክስ ዕዳው የተከፈለበትን ጊዜ መሰረት በማድረግ አስተዳደራዊ ቅጣቶች በከፊል የሚነሱት



Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

ቀጥሎ በተዘረዘረው መሰረት ቅጣቶችን በዝቅተኛ፣መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ በመመደብና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 በተደነገገው መስፈርትና መጣኔ ስንጠረዥ መሰረት ሆኖ፣

1. የታክስ አስተዳደር አዋጅ በስራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ የሚጣሉ አስተዳደራዊ መቀጫዎች በከፊል የሚነሱት፣

   ሀ) የአዋጁ አንቀጽ 101፣103፣104፣105፣ 107 (ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3) ፣ 109፣ 111፣ 112 እና 113(ንዑስ አንቀጽ 3) በዝቅተኛ የቅጣት ደረጃ ተመድበዋል፡፡

   ለ) የአዋጁ አንቀጽ 106፣ 113 (ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2) ፣ እንዲሁም አንቀጽ 114(ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 6) በመካከለኛ ደረጃ የቅጣት ደረጃ ተመድበዋል፡፡

   ሐ) የአዋጁ አንቀጽ 102፣ 107 (ንዑስ አንቀጽ 4) ፣ 108፣ 110፣ እና 114 (ንዑስ አንቀጽ 7) በከፍተኛ ደረጃ የቅጣት ደረጃ ተመድበዋል፡፡

2. የፌደራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በነበረ የታክስ ህግ መሰረት ግዴታን ባለመወጣት የሚጣል አስተዳደራዊ መቀጫዎች በከፊል የሚነሱት፣

   ሀ) ታክስን አሳንሶ በማሳወቅ ወይም ታክሱንም ያልሰበሰበ ወይም ደረሰኝ ሳይሰጥ የሰበሰበ እና ሳይመዘገብ ደረሰኝ በሚሰጥ ላይ የተጣሉ ቅጣቶች፣ ታክስን ባለማሳወቅ እና ዘግይቶ በመክፈል የተጣሉ ቅጣቶች፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሣሪያን ከመጠቀም ግዴታ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች፣ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ የአገልግሎት ማዕከል ጋር የተያያዙ ቅጣቶች በዝቅተኛ ደረጃ ተመድበዋል፡፡

   ለ) ከሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ወይም ሶፍትዌር አቅራቢ ጋር የተያያዘ ቅጣት እና የታክስ ደረሰኝ መስጠት ሲገባው ባለመስጠት የተጣሉ ቅጣቶች በመካከለኛ ደረጃ ተመድበዋል፡፡

   ሐ) መዝገብ አለመያዝ እና ሰነድ ባለማቅረብ የተጣለ ቅጣት በከፍተኛ ደረጃ ተመድበዋል ፡፡

## 6. የአስተዳደራዊ ቅጣት በከፊል የሚነሳበት መስፈርትና መጣኔ

ከላይ በአንቀጽ 5 በተደነገገት የቅጣት ደረጃዎችና የታክስ ዕዳው የተከፈለበትን ጊዜ መሰረት በማድረግ ቀጥሎ በተገለፀው መስፈርትና መጣኔ መሰረት አስተዳደራዊ መቀጫዎች በከፊል ሊነሱ ይችላሉ፡፡

በመቶኛ(%)

| ተ.ቁ | ፍሬ ታክስ፣ ወለድ እና መቀጫ የተከፈለበት ጊዜ | የቅጣት አነሳስ መጣኔ፣ በቅጣት ደረጃ ምደባ መሠረት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት | በመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት | በከፍተኛ ደረጃ የሚመደብ ቅጣት |
| 1 | ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ወይም የቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል ወይም የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ወይም የፍ/ቤት ውሳኔ በደረሰው፡- | | | |
| 1.1 | በ30 ቀናት ውስጥ ቀርቦ ከከፈለ | - | 80 | 70 |
| 1.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 80 | 70 | 60 |
| 1.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፊያ ጊዜ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| 2 | ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ ማስጠንቀቂያ ሳይደርሰው ሀብቱ ተይዞ ለግብር ዕዳው እንዲውል የሚገልጽ የመያዣ ትዕዛዝ ማስጠንቀቂያ ከመሰጠቱ በፊት ቀርቦ፡- | | | |
| 2.1 | በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 80 | 70 | 60 |
| 2.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 2.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፊያ ጊዜ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| 3 | ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ ሀብቱ ተይዞ ለታክስ ዕዳው እንዲውል የሚገልጽ የመያዣ ትዕዛዝ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ ሆኖ ሀብቱ ከመያዙ በፊት ቀርቦ፡- | | | |
| 3.1 | በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 70 | 60 | 50 |
| 3.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| 3.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 50 | 40 | 30 |
| 4 | ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ታክስ ባለመክፈሉ ሀብቱ የመያዝ ትዕዛዝ ከደረሰው ወይም ሀብቱ ከተያዘ በኋላ ሀራጅ ወይም ጨረታ ከመውጣቱ በፊት ወይም በኋላ ቀርቦ፡- | | | |
| 4.1 | በአንድ ጊዜ አጠቃሎ ከከፈለ | 60 | 50 | 40 |
| 4.2 | ባለስልጣኑ በሚሰጠው እስከ 6 ወራት በሚደርስ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 50 | 40 | 30 |
| 4.3 | ባለስልጣኑ በሚሰጠው ከ6 ወራት በላይ በሆነ የክፍያ ጊዜ ከከፈለ | 40 | 30 | 20 |

Ethiopian Revenue and Customs Authority
Records & Documentation No. 1

7. አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ የሚነሳበት ሁኔታ

1. ታክስ ከፋዩ የታክስ ግዴታውን በጊዜ እንዳይወጣ የሚያደርግ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ያገጠመው እንደሆነ፤
2. ድርጅቱ የንግድ ሥራ ሊቀጥል የማይችልና የከሰረ (bankrupt) መሆኑ በፍ/ቤት ሲረጋገጥ፤
3. ባለሥልጣኑ ሒሳቡን ከመመርመሩ በፊት ታክስ ከፋዩ በራሱ ተነሳሽነት ስህተቱን ያረመ እንደሆነ እና በተሻሻለው ስሌት ታክስና ወለድ ከከፈለ በዚህ ላይ የሚጣል ቅጣት መጠን፣
4. ከንብረቱ 20% እና ከዚያ በላይ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት የወደመበት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም ያቀረበ እንደሆነ፤
5. ከራሱ ገቢ ላይ ግብር ቀንሶ የሚያስቀር ተቀጣሪ በሥራ ላይ እያለም ሆነ የሥራ ውሉ ሲቋረጥ፤
6. የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ፍሬ ታክሱን፣ ወለድ እና በሌሎች የቅጣት ደረጃ የማይነሳውን ቅጣት ሙሉ ለሙሉ ከከፈለ በታክስ ውሳኔው ውስጥ የሚገኝና በዝቅተኛ ደረጃ የተመደበ አስተዳደራዊ ቅጣት ካለ፤
7. ለቅጣቱ ምክንያት የሆነው ባለስልጣን መ/ቤቱ በፈጠረው የአሰራር ስህተት መሆኑ ከተረጋገጠ፣

አስተዳደራዊ ቅጣቱ ሙሉ በሙሉ ይነሳል።

8. የቅጣት ይነሳልኝ ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት

አስተዳደራዊ ቅጣት የተወሰነበት ሰው ቅጣቱ እንዲነሳለት ምክንያቱን በመግለጽ ለባለስልጣኑ ቅ/ጽ/ቤት ለታክስ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥራ ሂደት በጽሑፍ ማመልከት አለበት።

9. ቅጣትን የማንሳት ሥልጣን

1. የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት መሪ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 እና 7 መሰረት ቅጣቶችን ያነሳል።
2. የተነሳው ቅጣት ስለመነሳቱ በተዘጋጀ ቅጽ ተሞልቶ በሥራ ሂደቱ ከተረጋገጠና ከጸደቀ በኋላ የሚከፈለው ታክስ፣ ወለድና የማይነሳው ቅጣት መጣኔ ተከፍሎ

ቀሪው መቀጫ ዕዳውን በሚከታተለው የዕዳ ክትትልና አሰባሰብ ባለሙያ ከሲስተም (SIGTAS) ላይ ተገቢው መግለጫ ሰፍሮ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ክትትል የሥራ ሂደት መሪ በሚወስነው የቅጣት አነሳስ ላይ በታክስ ከፋይ የሚቀርብ ቅሬታ በቅ/ጽ/ቤቱ የተቋቋመው የቅሬታ አጣሪ ሥራ ክፍል በመቀበል መርምሮ ለቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ ያስወስናል፡፡ በውሳኔው መሰረት ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

## 10. አስተዳደራዊ ቅጣትን በልዩ ሁኔታ ስለማንሳት

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 ፣ 6 እና 7 ላይ የተመለከተው ቢኖርም በኢኮኖሚያዊ፣ አስተዳደራዊ ወይም ማህበራዊ ምክንያቶች የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም በሚወክለው ኃላፊ በልዩ ሁኔታ በታክስ ከፋዩ ጥያቄ ወይም ባለሥልጣኑ በራሱ ተነሳሽነት አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ሊያደረግ ይችላል፡፡

2. ለባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ለሚወክለው ኃላፊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ የሚቀርብ ጉዳይ ዝርዝር የውሳኔ ሀሳብ በአገር ውስጥ ታክስ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት እንዲቀርብበት ተደርጎ፣ የቀረበው ምክንያት አሳማኝ ሆኖ ከተገኘ የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም የሚወክለው ኃላፊ አስተዳደራዊ ቅጣት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3. ለዋና ዳይሬክተሩ ወይም ለወከለው ቀርቦ በሚወሰነው መሰረት እንዲፈፀም በአገር ውስጥ ታክስ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት በኩል ለቅ/ጽቤቱ የሚላክ ሆኖ የሚነሳው አስተዳደራዊ መቀጫ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9(2) መሠረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 11. በክፍያ ስምምነት ጊዜ የቅጣት አነሳስ

1. በክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ መሰረት የታክስ ዕዳውን በተራዘመ ጊዜ እንዲከፈል ለማድረግ ከግብር ከፋዩ ጋር በሚደረግ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል ውስጥ ከፍሬ ታክስና ወለድ በተጨማሪ በመቀጫ አነሳስ መመሪያ መሠረት

የማይነሳውን መቀጫ(በከፊል ተነስቶ ከፊሉ ሳይነሳ በሚቀርበት ሁኔታ) ብቻ ጨምሮ ሊነሳ የሚችለው መቀጫ እንዳይካተት ሊደረግ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 በተገለጸው አግባብ ግብር ከፋዩ በስምምነቱ መሰረት ፍሬ ታክሱንና ወለዱን ከፍሎ ማጠናቀቁ ሲረጋገጥ መቀጫው እንዲነሳ ይደረጋል።
3. በስምምነቱ መሰረት ግዴታውን ካልተወጣ ቅጣቱ በቀጣይ ባልተከፈለ የታክስ ዕዳ መጠን መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. ወለድ የማይነሳ ስለመሆኑ

1. በፌዴራል ገቢ ግብር እና በሌሎች የታክስ አዋጆች መሰረት በዘገየ የታክስ ክፍያ ላይ የሚታሰብ ወለድ በዚህ መመሪያ መሰረት የሚነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በሕግ ወለድ መስላት በሌለበት በታክስ ጉዳይ ላይ በታክስ መረጃ ሥርዓቱ (ሲስተም) ባህሪ የተነሳ ተሰልቶ የሚገኝ ወለድ ጉዳዩ በሚመለከተው ባለሙያ መግለጫ እንዲቀርብ ተደርጎ ከሲስተም ላይ እንዲሰረዝ በስራ አስኪያጅ ሲወሰን ከሲስተም ላይ ተገቢው መግለጫ ሰፍሮ እንዲሰረዝ ይደረጋል፡፡

13. በዚህ መመሪያ የማይነሳ አስተዳደራዊ ቅጣት

1. የታክስ ባለስልጣኑ በሕግና በውክልና በሚሰበስባቸው የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት እና የጡረታ መዋጮ ክፍያ ግዴታን ባለመወጣት የሚጣል መቀጫ በዚህ መመሪያ መሰረት የሚነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም፡፡
2. በቀድሞው የገቢ ግብር አዋጅ 286/94 አንቀጽ 90(1) እና አንቀጽ 91 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ በተመለከተው መሠረት የተጣለ ቅጣት በዚህ መመሪያ መሰረት የሚነሳ ወይም ቀሪ የሚደረግ አይሆንም፡፡

14. ሪፖርት ስለማቅረብ

1. በቅ/ጽ/ቤቶች በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ፣ 7 እና 10 ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሱ ውሳኔ የተሰጣቸው አስተዳደራዊ መቀጫዎቹ የተነሳውን

የመቀጫ የገንዘብ መጠን በየወሩ ተጠናቅሮ ከወርሃዊ ሪፖርት ጋር በግልጽ ተለይቶ ለባለስልጣኑ የፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት መቅረብ አለበት፡

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 በተመለከተው መሠረት ቅ/ጽ/ቤቶች ሪፖርታቸውን በወቅቱ እንዲልኩ የፕላንና ፕሮጀክት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ክትትል ያደረጋል፤ እንደአስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው ዘርፍ ሪፖርት ያደርጋል።
3. ባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲነሳ ውሳኔ የሰጠበትን የእያንዳንዱን መዝገብ መረጃ ከየቅርንጫፍ ጽ/ቤት በማጠናቀር በየሩብ ዓመቱ የተጠቃለለ ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማቅረብ አለበት።

## 15. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

በሥራ ላይ የነበረው መመሪያ ቁጥር 55/2003 አስተዳደራዊ ቅጣቶች ስለሚነሱበት ሁኔታ የሚገልጹ ድንጋጌዎች እና ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ህግ፣ ሰርኩላርና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

## 16. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ መመሪያ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በመመሪያ ቁጥር 55/2003 መሰረት ተቀባይነት አግኝቶ የታክስ ክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት ውስጥ ገብቶ የታክስ ዕዳውን በመክፈል ላይ የሚገኝ ግብር ከፋይ የአስተዳደራዊ ቅጣት አነሳስ ጉዳይ በነባሩ መመሪያ መሠረት ፍጻሜ ያገኛል።

## 17. መመሪያው የሚሻሻልበት ሁኔታ

ይህ መመሪያ የሚሻሻለው መመሪያ ለማውጣት ስልጣን ባለው አካል ተሻሽሎ ሲወጣ ብቻ ይሆናል።

## 18. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከነሀሴ ------- ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሀሴ 2010 ዓ.ም

**ዑመር ሁሴን**
**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር(ሚኒስትር)**